# እውነተኛው እና ሐሰተኛው ወንጌል

ዛክ ፑነን

ክርስቲያኖች የሚያተኩሩበትን ነገሮች ስናጠና አብዛኛውን ጊዜ በሁለት ክፍሎች እንመድባቸዋለን።

1. “ሮማን ካቶሊኮች” እና “ፕሮቴስታንቶች” – እንደ ትውልዳቸው
2. “ኢጲስ ቆጶስ” (በጳጳስ የሚተዳደሩ) እና “ነፃ አማኞች” (በጳጳስ የማይተዳደሩ) - እንደ ቤተ ክርስቲያን አመራራቸው
3. “ዳግመኛ የተወለዱ” እና “የስም ክርስቲያኖች” – እንደተለማመዱት የልብ መለወጥ
4. “ወንጌላዊ” እና “ስለ መፅሐፍ ቅዱስ የላላና ሁሉንም የመመ፡ቀበል ትርጉም የሚከተሉ” - እንደ ሥርዓታቸው
5. ስለ ልሳን እንዳላቸው አመለካከት “በልዩ ልሳን የሚናገሩ” እና “ በልዩ ልሳን የማይናገሩ” -
6. “የክርስቲያን ስራ ሙሉ ጊዜ የሚሰሩ” እና “አለማዊ ስራ ውስጥ የሚገኙ” - እንደ ሞያ ልምዳቸው

ሌሎች አመዳደቦችም ሊኖሩ ይችላሉ። ሆኖም ግን ማናቸውም አመዳደቦች ጌታችን ሊፈታው የ መጣበትን መሰረታዊ ችግር አይመረምሩም።

አብዛኞቻችን “ክርስቶስ ለሃጥያታችን እንደሞተ እናውቃለን (1 ቆሮ 15:3)።ነገር ግን እርሱ የሞተው ለሃጥያታችን ብቻ ሳይሆን ‘ለእኛ ሲል ለሞተውና ከሞትም ለተነሳው እንድንኖር እንጂ ከእንግዲህ ወዲህ ለራሳችን እንዳንኖር’ መሆኑን መፅሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምር አልተረዳንም (2 ቆሮ 5:15) ።እንግዲህ በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሰረተ የክርስቲያኖች አመዳደብ እንደሚከተለው ነው፤“ለራሳቸው የሚኖሩ” እና “ለክርስቶስ የሚኖሩ” ፡ ወይም “የራሳቸውን የሚፈልጉ” እና “ የክርስቶስን ነገሮች የሚፈልጉ” ፡ ወይም “ምድራዊ ነገሮችን የሚያስቀድሙ” እና “የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያስቀድሙ”፡ ወይም “ገንዘብን የሚወዱ” እና “እግዚአብሔርን የሚወዱ” (እየሱስ ሁለቱንም ማገልገል እንደማይቻል በሉቃስ 16:13 ተናግሯል)።ይሄን የመሰለ አመዳደብ ግን ሰምቼ አላውቅም። ይሄ ከላይ የተጠቀሰው ሁለተኛው አመዳደብ የሚያተኩረው በማይታየው በክርስቲያን የተደበቀ ኑሮ እና ከእግዚአብሔርም ጋር ባለው የግል የአምልኮ ህይወቱ ላይ ሲሆን በመጀመሪያ የተጠቀሰው አመዳደብ ግን ለሰው በሚታየው በክርስቲያኑ ውጫዊ ኑሮ ላይ ያተኮረ ነው። መንግሥተ ሰማይም ክርስቲያኖችን የሚመድበው በዚህ በሁለተኛው መንገድ ወይም በውስጣዊ ሕይወታችን መሠረት ነው።እንዲህም ከሆነ የሚጠቅመን ይህ ሁለተኛው አመዳደብ ብቻ ነው። ምክንያቱም ውስጣዊ ምኞታችንን የሚያነቃቃው ምን እንደሆነ ከራሳችን በቀር የገዛ ሚስቶቻችን እንኳን ሊያውቁት አይችሉም።ጌታችን ወደ ምድር የመጣበት ዋናው ምክንያት የቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓትን ለመስጠት ወይም ሰዎችን በልዩ ልሳን እንዲናገሩ ለማድረግ ወይም ደግሞ የተለየ እውቀትን ለመስጠት አይደለም።

እሱ ወደ ምድር የመጣው ‘ከሃጥያታችን ሊያድነን ነው’። ምሳርን በዛፉ ስር ሊያስቀምጥ መጥቷል። የዚህም የዛፍ ስር ሃጥያት ነው።ይሄውም ራሳችን ላይ ማተኮር፣ ለግላችን የሚሆነውን ማሳደድና የራሳችንን ፍላጎት ማርካት ነው።ጌታ ምሳሩን ተክሎ ይሄንን የሃጥያት ስር ከህይወታችን እንዲነቅል ካልፈቀድን ክርስትናችን የላይ ላዩን የሆነ

የስም ክርስትና ብቻ ይሆናል።ሆኖም ሰይጣን ስለምንከተለው ሕግና ሥርዓት ወይም በተቀበልነው ልዩ እውቀት ላይ እንድናተኩርና እራሳችንንም ከሌሎች ክርስቲያኖች ከፍ አድርገን እንድናስብ ሊያታልለን ይችላል።ሰይጣን 'ለራሳችን እስከኖርን' ድረስ (ይህም በሃጥያት መኖርን የሚያመለክት አነጋገር ነው) የምንከተለው ሕግና ሥርዓትም ሆነ የኛ የተለየ እውቀት ግድ አይሰጠውም።ክርስትና በአሁኑ ጊዜ የራሳቸውን በሚሹ እና ለራሳቸው በሚኖሩ፣ ስለሚከተሉት የቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት ወይም ስለተቀበሉት ልዩ እውቀት እግዚአብሔር ከሌሎች ክርስቲያኖች የተሻሉ ሆነው እንደሚያያቸው በሚያምኑ ሰዎች ተሞልቷል።ይሄም ሰይጣን በክርስትና ላይ የሰራው ሐሰታዊ ስራ ምን ያህል እንደተቃናለት ያሳያል።

በዮሐንስ 6:38 እንደምንረዳው ጌታችን ከሰማይ ወደ ምድር የወረደው፣

1 የራሱን ፈቃድ ለመካድ (ሰውን መስሎ ወደ ምድር ሲወርድ ያገኘውን ፈቃድ) እና
2 የአባቱን ፈቃድ በሰውነቱ ለመፈፀም ነው። ስለዚህም ምሳሌያችን ሆኗል።

በእየሱስ ምድራዊ ህይወት ሁሉ ማለትም በኖረበት በ33 ½ አመታት የራሱን ፈቃድ ክዶ የአባቱን ፈቃድ ፈፅሟል። ለደቀመዛሙርቱም እውነተኛ ደቀመዛሙርቱ መሆን ከፈለጉ በዚህ ረገድ እሱን መከተል እንዳለባቸው በግልፅ ነግሯቸዋል።ስለዚህም የሃጥያትን ስር ከህይወታችን ለመንቀል ማለትም "የራሳችንን ፈቃድ ከመፈፀም" ሊያድነን መጥቷል።

በሳይንስ ለሰው ዓይን ፀሃይ ጨረቃና ከዋክብት ምድርን በየ24 ሰዓቱ የሚዞሩ ስለሚመስል ለብዙ ሺህ ዓመታት ምድር የዓለማትን መሀከላዊና ዋና ቦታ ይዛለች የሚል የተሳሳተ አስተያየት ነበር። ይሄንንም ዝነኛ አስተያየት ለመፈተን ኮፐርኒከስን የመሰለ ደፋር ሰው ያስፈልግ ነበር።ከዛሬ 450 ዓመት በፊት ይሄ አስተያየት ፈፅሞ ሐሰት እንደነበር እና ምድርም የዓለማትን መሀከላዊና ስፍራ እንዳልያዘች አሳይቷል።ኮፐርኒከስ የዓለማችን መሀከላዊ ቦታ ፀሀይ እንደሆነችና ምድርም የተፈጠረችው ፀሀይ ጨረቃና ከዋክብት እሷን እንዲዞሩ ሳይሆን ምድር እራሷ ፀሀይን እንድትዞር መሆኑን አረጋግጧል።እንግዲህ ሰው የተሳሳተ ነገር ላይ ትኩረት እስከሰጠ ደረስ የሳይንስ ስሌቱና ትንተናው የተሳሳተ ነበር።ነገር ግን ሰው ትክክለኛውን መሃከላዊ ፍጠረት ካወቀ በኋላ እነዚህ ድምርና ትንተናዎች ተስተካከለዋል።

በተመሳሳይ መንገድ "እግዚአብሔር ላይ በማተኮር" ፈንታ "በራሳችን ላይ ስናተኩር" በህይወታችን እንሳሳታለን። ስለ መፅሐፍ ቅዱስም ሆነ ስለ እግዚአብሔር ፍፁም ፈቃድ ያለን አመለካከት (ስሌትና ትንተናችን) የተሳሳተ ይሆናል።ግን ቀደም ብሎ በተጠቀሰው ምሳሌ ሰው ከአምስት ሺህ ዓመታት በላይ የተሳሳተ አመለካከቱን እንደ እውነት እንደተቀበለው እኛም እንደዚሁ የተሳሳተ አመለካከታችን ትክክል እንደሆነ ልናምን እንችል ይሆናል። እውነቱን ስናውቅ ግን መቶ በመቶ እንደተሳሳትን እንረዳለን።ዛሬ በብዙ 'ጥሩ ክርስቲያኖችም' የምናየው ይሄንን ነው።ሁሉም ስለ አንዱ መፅሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ትርጉሞች ይይዙና ሁሉም የራሳቸው አተረጓጎም ትክክል እንደሆነ በማመን ሌሎችን እንደ "ተታለሉ" አድርገው ይቆጥሯቸዋል።ለምን እንደዚህ ሆነ? እነዚህ ክርስቲያኖች ትኩረት የሰጡት በተሳሳተ ነገር ላይ ስለሆነ ነው።ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር ላይ እንዲያተኩር እንጂ በራሱ ላይ እንዲያተኩር አይደለም።ሰለዚህ ክርስቲያኖች የተሳሳተ ነገር ላይ ሲያተኩሩ "ወንጌላቸውም" ይሳሳታል።በመሠረቱ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ሁለት ወንጌሎች እየተሰበኩ ነው።አንደኛው ሰው ላይ የሚያተኩር ወንጌል ሲሆን ሌላው እግዚአብሔር ላይ የሚያተኩር ወንጌል ነው።

ሰውን ዋና ትኩረት የሚሰጠው ወንጌል እግዚአብሔር ለሰው ኑሮውን የሚያመቻችለትን ነገር ብቻ ሳይሆን በመንግስተ ሰማይም ቦታ እንደሚሰጠው ያስተምራል። ሰዎች እየሱስ ሃጥያታቸውን ሁሉ ይቅር ብሎ በሽታቸውን እንደሚያድንላቸው፣ በምድራዊ ሀብት እንደሚባርካቸውና ማናቸውንም ችግር እንደሚፈታላቸው ወዘተ... ይማራሉ።

ሰው (ራስ) መሀከለኛ ትኩረት ይይዝና እግዚአብሔር እንደ አገልጋይ በሰው ዙሪያ እየተመላለሰ ለሰው ፀሎት ይታዘዛል። ሰው የፈለገውን ነገር ሁሉ ለማገኘት ማድረግ ያለበት ነገር ቢኖር በእየሱስ ስም “ማመንና” ስለሚፈልገው ነገር “በቃሉ መናገር” ብቻ ነው።እንደዚህ ዓይነቱ ወንጌል “ንስሃ ስለመግባት” ምንም ስለማይጠቅስ ሐሰታዊ ወንጌል ነው።መጥምቁ ዮሐንስ፣እየሱስ፣ጳውሎስ፣ጴጥሮስና ሐዋርያቶቹ ሁሉ ንስሃን የስብከታቸው መጀመሪያ ያደርጉት ነበር።በአሁኑ ጊዜ ግን በሚያሳዝን ሁኔታ ንስሃ በስብከት መጨረሻ እንኳን አይጠቀስም።

በአንፃሩ እግዚአብሔር ላይ የሚያተኩር ወንጌል ሰዎችን ንስሃ እንዲገቡ ይጠራል። ንስሃ መግባትም ምን ማለት እንደሆነ በግልፅ ያስረዳል። ይኼውም - የራሳችን ህይወት ላይ ከማተኮር፣የራሳችንን ፈቃድ ከመፈፀም፣እራሳችን በመረጥነው መንገድ ከመሄድ፣ገንዘብንና ዓለምን ከመውደድ እና ከዓለም ነገሮች (የስጋ ምኞት የዓይን አምሮትና የኑሮ ትምክህት) ወዘተ... በመቆጠብ ወደ እግዚአብሔር እየተመለስን በሙሉ ልባችን እንድናገለግለውና ከእንግዲህ ወዲህም ህይወታችን በሱ ላይ እንዲያተኩር ያስተምረናል።በክርስቶስ የመስቀል ሞት ማመን ለሰው ሃጥያት ይቅርታን የሚያስገኘው ያ ሰው ንስሃ ከገባ በኋላ ብቻ ነው።ያኔ ሰው የራሱን ፈቃድ በየቀኑ እየካደ በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ የሚያተኩር ህይወትን መኖር የሚያስችለውን የመንፈስ ቅዱስን ሃይል መቀበል ይችላል።እየሱስና ሐዋርያቶቹም የሰበኩት ወንጌል ይሄንኑ ነበር።

ሐሰታዊ ወንጌል የመዳንን በር ሰፊ መንገዱንም ትልቅ ያደርገዋል (በዚህ በር ለመግባት ራስን መካድም ሆነ ለራስ ከመኖር፣የራስን ፍላጎት ከማሳደድና የራስን ትርፍ ከመሻት ማንም መቆጠብ ስለሌለበት ሰዎች በቀላሉ ይገቡበታል)።በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦች ይኼን ሐሰታዊ “ወንጌል” ሲሰበክ ለመስማት ይመጣሉ።ብዙዎችም እንደዚህ ዓየነቱ ትምህርት ወደ ህይወት እንደሚመራቸው በማመን በዚህ ሰፊ በር ገብተው በመንገዱ ይጓዛሉ። በእርግጥ ግን ይሄ መንገድ የሚመራቸው ወደ ጥፋት ነው።የዚህ ወንጌል አስተማሪም በሚያቀርበው ሪፖርት ላይ በስብሰባው ምን ያህል ሰዎች “እጃቸውን አንስተው ክርስቶስን ለመቀበል እንደወሰኑ” በመጠቆም ለትምክህት ይጋበዛል።ይሄ ሁሉ ግን መታለል ነው።ምንም እንኳን አንዳንዶቹ ከልባቸው ቅንነት የተነሳ በእርግጥ ቢለወጡም ብዙዎች ሌሎች ‘አማኞች’ ግን በመጨረሻው ‘በእጥፍ የባሰ የገሃነም ልጅ’ (ማቴዎስ 23:15) መሆናቸውን ባለማወቅ ስለእውነተኛ ሁኔታቸው እንደተታለሉ ይቀራሉ።

እውነተኛው ወንጌል በአንጻሩ የመዳንን በሩን ጠባብ መነገዱንም ቀጭን ያደርገዋል።ይኼንንም በር አንዳንድ ‘ጥራዝ ነጠቅ መንፈሳዊያን’ እንደሚያደረጉት እየሱስ ካጠበበው የበለጠ እንዳያጠቡት አስተማሪዎቹ ይጠነቀቃሉ። ይኼንንም የሕይወት መንገድ የሚያገኙት ጥቂቶች ናቸው።ይኼንን እውነተኛ ወንጌል ለሚሰብክ ወንጌላዊ ሪፖርቱን በሚያስደንቁ ቁጥሮች የሚሞላበት ብዙ ነገር ባይኖረውም የሚሰብከው ወንጌል ሰዎችን ወደ መንግስተ ሰማይ ይመራል።ስለዚህ ‘እንዴት እንደምትሰሙ ተጠንቀቁ’። ማነኛውም ለሰማው ነገር የሚታዘዝ ለእርሱ የበለጠ ብርሃንና የበለጠ እውቀት ይሰጠዋል።ማንም ግን ለሰማው ነገር የማየታዘዝ ያለው የሚመስለው ብርሃንና እውቀት እንኳን ከእርሱ ይወሰድበታል’ (ሉቃስ 8:18 በቀላሉ ሲተረጎም)። ጆሮ ያለው ይስማ።

*[The True Gospel and the False – (Amharic – Ethiopian)]*

**By Zac Poonen**